# ያልደረሱትን እረሳን!




ሲዳሩ ማልቀስ አሁንም፤ ወግና ማረግ ሆኖብን፣
አሩግ መሆኑን እያወቅን፤ ታዲሱ ዘመን ገባን አልን።

የጷጉሜ ጠበል ሳይነካን፤ ያደፈ ቆዳ ለብደን፣
ዛሬም እንደ ትናንቱ ተሻገርን፤ የሰው ደም በእግር እረግጠን።

ፍትህ ተምድር ተቀብራ፤ ነፍስ አጥፊ አገር ሲገዛ፣
ቀኑ እንደ ደመና ጨልሞ፤ ተሰደን መግቢያ ስናጣ፣
ሌሊቱን እንዴት አልፈነው፤ ነጋና መስከረም ጠባ?

እምነት ሳይሽረው ክህደትን፤ ሱባኤ ሳያጥብ ወንጀልን፣
ንስሀ ሳይጠርግ ሐጥያትን፤ እርቅ ሳይፍቀው በደልን፣
እንዴት ተሻግረን ክረምቱን፤ መስከረም ጠባ እልል አልን?

እንደ ቅድመ-አያት ሳንቆርጥ፤ ወጉ ባህሉ ሳይገባን፣
በሰላም ደረስን ተባባልን፤ ስንቱን ህፃናት ለጭራቅ ገብረን።

ሆ ሄ በላቲን ተፍቆ፤ ቤተ-ክርስትያን ተደፍሮ፣
አስራት ከፋዩ ምዕመን፤ በሰይፍ አንገቱ ተቀልቶ፣
ለአላህ ሲሰግድ አማኙ፣ ተነመስጊዱ ተቃጥሎ፣
የምን ከበሮ ድለቃ፤ ቆብን ቆልሎ ሻሽ አስሮ።

በሳጥናኤል እግር ተጉዘን፤ ሰማእታትን ዘንግተን፣
እምብርት እስቲፈነዳ ጎስጉሰን፤ ጥንብዝ እስትንል ጠጥተን፣
ስንባባል አናፍርም፤ እንኳንም በሰላም ደረስን፣
እንደ በግ የታረደውን፣ እልፍ አእላፉን እረግጠን።

የአድራሹን ትዕዛዝ በጥሰን፤ በይሁዳ ጫማ ተጉዘን፣
ሰማእታትን ካድ አርገን፣ ተሰዋቸው ጋር ተጣብቀን፣
መልካምን ዘመን መመኘት፤ ቆዳና ልብን አጉድፈን።

አሮጌው ዓመት ቀፍድዶን፤ አዲሱ ተሰማይ እርቆን፣
ተመንዘላዘል የማንድን፤ ማወቅ የማንችል እባብን፣
በቀትር ፀሐይ የምንሄድ፤ ቅቤ ታናት ላይ አኑረን፣
አድሮ ቃሪያዎች ትሉሎች፣ ማሞ ቂሎዎች ከብቶች ነን።

መሞት ማለፍን ዘንግተን፤ ሰማእታትን የረሳን፣
ተገዳዮች ጋር የደለቅን፤ ደመ-ነፍስ እንኳን ያልገታን፣
እንሰሳም ሊሉን የከበድን፣ አምላክ ያስቸገርን ፍጡር ነን።

ሆድና ስስት ማርከውን፤ አድርባይነት አጣሞን፣
ሕዝብን ታስፈጁት ጭራቆች፤ አብረን ዶልተን የጨፈርን፣
ለእኛ ሲል የሞተው ሁሉ፤ መቃብር ከፍቶ የሚያየን፣
ታሪክ ሲወቅሰን የሚኖር፣ ተተኪ ትውልድ ሲያፍርብን፣
ጥቅምና ፍርሃት የገዛን፣ የእሳት ልጅ አመድ ከንቱ ነን።

በመድረሳችን ተሳክረን፤ ያልደረሱትን የረሳን፣
በደም ጎርፍና ኩሬ ተነክረን፣ በሰላም ደረስን የደለቅን፣
ጡት እንደሚጠባ እምቡቅል፤ ክፉና ደጉን ያለየን፣
የሚያስት እባብ የማናውቅ፤ ዓይኖች ያልገለጥን ድመት ነን።

Please read the document here and look at link the pictures of some of the victims of EPRDF: https://www.ethiomedia.com/carepress/yared_testimony.pdf

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
መጀመርያ መስከረም አንድ ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.
እንደገና መስከረም አስራ ስድስት ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓ.ም